# የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት የዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ

## ትምህርት ሚኒስቴር

መስከረም 2003
አዲስ አበባ

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. መግቢያ

በኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር የፌዴራል አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/1998 አንቀፅ 14/2፣ 3 እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 650/2001 አንቀፅ 97/2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የትምህርት አግባብነት እና ጥራትን ለማስጠበቅ ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 2. የመመሪያው አስፈላጊነት

ይህን መመሪያ ማውጣት ያስፈለገው የሚከተሉትን ዓላማዎች ለማሳካት ነው።

1) መንግስት በተለይ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ የስልጠና ዘርፎች ያስቀመጠውን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ብቁ፣ ተወዳዳሪና ገበያው የሚፈልገውን የሰው ሃይል በማፍራት የታቀደውን ልማት ቀጣይነት ማረጋገጥ፣
2) የትምህርትና ስልጠና ጥራት የማረጋገጥ ሂደት ውጤትን፣ ሂደትንና ግብዓትን ማዕከል በማድረግ የሚሰራበትን የተጠናከረ ስርዓት መዘርጋት፣
3) ተቋማት ጥራት ያለው ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት ያላቸውን ብቃትና ዝግጁነት በየጊዜውና ቀጣይነት ባለው መልኩ እየፈተሹና እያጠናከሩ መሄድ የሚችሉበትን ስርዓት መዘርጋት፣

## 3. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “በግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሰጥ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት የዕውቅና አሰጣጥ መመሪያ መስከረም 2003” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 4. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1) "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ነው።
2) "ሚኒስቴር" ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው።
3) "የከፍተኛ ትምህርት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 8 የተመለከተውን ትርጉም ይይዛል።
4) "ኤጀንሲ" ማለት የትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ነው።
5) "ተቋም" ማለት የከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥ የግል ወይም መንግስታዊ ያልሆነ አካል ነው።
6) "የዕውቅና ፈቃድ" ማለት ትምህርትና ሥልጠና ለመጀመር በአዋጁ መሰረት ለተቋም የሚሰጥ የስራ ፈቃድ ነው።
7) "የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት" ማለት ትምህርትና ስልጠና እንዲቀጥል በአዋጁ መሰረት ለተቋም የሚሰጥ የእድሳት ፈቃድ ነው።
8) "የማስተማሪያ መጽሐፍ" ማለት አንድ ትምህርት (ኮርስን) ለማስተማር የሚረዳ ሰፋ ያለና ዝርዝር መረጃዎችን የያዘና ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲጨብጡ የሚረዳ መፅሐፍ ነው።
9) "የማጣቀሻ መጽሐፍ" ማለት ሊሰጥ ለታሰበው ትምህርት (ኮርስ) የመረጃ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል ሁሉ አቀፍ መጽሐፍ (Reference book) ነው።
10) "ሳይንቲፊክ ጆርናል" ማለት ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶችንና የሳይንሳዊ ጥናቶች ሙያዊ ግምገማዎች የሚታተሙበት ታዋቂ መጽሔት ነው።
11) "የማታ ትምህርት" ማለት በማታው እና በተጨማሪም በሳምንቱ የመጨረሻ ቀናት የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም ማለት ነው።

## 5. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጸድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በማንኛውም ተቋም ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## 6. ዝርዝር መመዘኛዎች

የዚህን መመሪያ ማስፈጸሚያ ዝርዝር መመዘኛዎችና የጥራት ደረጃዎች ኤጀንሲው ያወጣል።

# ክፍል ሁለት
# የእውቅና እና የእውቅና ፈቃድ ዕድሳትን ለማስተናገድ የሚያገለግሉ መሰረታዊ ነጥቦች

## 7. መርሆዎች

በዲግሪ ፕሮግራም ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት ተፈጻሚነት ያላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በተለይም

1) ትምህርቱ ወይም ሥልጠናው ከሃይማኖት ነፃ የሆነ ወይም ሴኩላር መሆን ይኖርበታል፤
2) ትምህርቱ ወይም ሥልጠናው የሚሰጥበት ቋንቋ እንግሊዝኛ ይሆናል፣
3) ማንኛውም ተቋም ተማሪዎችን የሚቀበልበት ሥርዓት በሃይማኖት፣ በብሔር በፆታና በመደብ ልዩነት የማይደረግበት ይሆናል፤
4) ተቋሙ የዕውቅና ፈቃድ ወይም የዕውቅና ፈቃድ እድሳት የሚጠይቅባቸው የትምህርትና ስልጠና መስኮች በአገሪቱ የሰው ኃይል ገበያ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ይሆናል፤
5) ተቋሙ ማስተማር የሚችለው የዕውቅና ፈቃድ እና የዕውቅና ፈቃድ እድሳት በተሰጠው የትምህርት ዓይነትና መጠን ልክ ብቻ ይሆናል፤
6) የተቋሙ ስያሜ በአዋጁ ለደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት የሚመጥን ይሆናል፤ በኤጀንሲውም ይረጋገጣል፤
7) ተቋሙ የሚያካሂደው የምርምር ሥራ የአገሪቱን እድገትና ልማት የሚያፋጥን፣ የሚያስቀጥልና ችግር ፈቺ መሆን ይኖርበታል፤
8) በማታው መርሃ-ግብር የሚሰጥ ትምህርት ራሱን የቻለ የእውቅና ፈቃድ ይኖረዋል፤ የሚሉትን መሰረታዊ መርሆዎችን የተከተለ ይሆናል።

## 8. የተማሪዎች ቅበላ መስፈርት

ማንኛውም ተቋም ተማሪዎችን የሚቀበለው በአዋጁ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ 3(ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) በተደነገገው መሰረት

1) የመሰናዶ ትምህርት ያጠናቀቁትንና ሚኒስቴሩ የሚያስቀምጠውን የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና የመቁረጫ ነጥብ የሚያሟሉትን፣

2) በውጭ አገር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቀው በኤጀንሲው የአቻ ግምት የተሰጣቸውን እና
3) ከቴክኒክና ሙያ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመሸጋገሪያ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟሉትን

ይሆናል።

## 9. ትምህርቱ ወይም ሥልጠናው የሚሰጥበት ህንጻና ከባቢ ሁኔታ

1) ተቋሙ ትምህርቱን ወይም ሥልጠናውን የሚሰጥበት ሕንፃና ግቢ በተቋሙ በግል ንብረትነት የተያዘ ወይም በማናቸውም በሕግ ፊት ሊጸና በሚችል ውል ለ5 ዓመታት እንዲያገለግል በኪራይ የተያዘ መሆኑ፤
2) መማሪያው ሕንጻና ግቢው ለመማር ማስተማር ምቹ እና መማር ማስተማሩን ወይም የተማሪዎችና የመምህራን ጤንነት ለሚያውኩ ሁኔታዎች ባልተጋለጠ ከባቢ መሆኑ፣
3) ተቋሙ ያለበት የመሬት አቀማመጥ ለጎርፍ፣ ለከባድ ንፋስ፣ ለፍሳሽና ሌሎች አደጋዎች ያልተጋለጠና ምቹ የመኪና መንገድ ያለው መሆኑ፤
4) ለተቋሙ ሠራተኞችና ተማሪዎች የተሰሩ በቂ የመጸዳጃ ክፍሎች፣ የመጀመርያ የሕክምና እርዳታ መስጫ ማዕከልና የጊዜ ማሳለፊያና መዝናኛ ክበቦች ያሉት መሆኑ እና
5) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቁ ሆኖ ተቋሙ የቦታ ለውጥ ከማድረጉ በፊት በኤጀንሲው ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል።

## 10. ክፍያ

የዕውቅናና የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ የኤጀንሲው ቦርድ በሚያወጣውና ሚኒስትሩ በሚያጸድቀው የክፍያ መመሪያ መሰረት ይፈጸማል።

## 11. ስለ ዕውቅናና ዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አስፈላጊነት

የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማሳደግ፣ ለመለወጥ ወይም ዕውቅና በተሰጠው ለመቀጠል ወይም አዲስ የትምህርት ዓይነት ለመክፈት የሚፈልግ ማንኛውም ተቋም በአዋጁና በዚህ መመሪያ የዕውቅና ፈቃድ ሳያገኝ የከፍተኛ ትምህርት ሊሰጥ አይችልም።

# ክፍል ሶስት

# የዕውቅና ፈቃድ አሰጣጥ መገምገሚያ መስፈርቶች

## 12. የዕውቅና ፈቃድ አገልግሎት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማሳደግ ወይም ለመለወጥ ወይም ተጨማሪ ካምፓስ ለመክፈት ወይም አዲስ መርሃ-ግብር/ፕሮግራም ለመክፈት ወይም በተፈቀደለት የተማሪዎች ብዛትን ለመጨመር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የያዘ የዕውቅና ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል። የሚቀርበው ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ 75 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆኖ

1) ለተቋሙ ደረጃ የሚመጥን አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ አደረጃጀት፣
2) ተቋሙ ለሚያቀርበው የስያሜ ደረጃ  አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እና
3) የሕንጻ የይዞታ ማስረጃ ወይም የአምስት ዓመት የኪራይ ውል ማቅረብ ይኖርበታል።

## 13. የዕውቅና ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት ትምህርትና ሥልጠና ለመስጠት የተዘጋጀ ተቋም ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው።

1) ተቋሙ በአንድ የትምህርት ዘመን በአንድ መርሃ-ግብርና የትምህርት ዓይነት ከተፈቀደለት ቁጥር በላይ ተቀብሎ ለማሰልጠን ከፈለገ የሚጠበቀውን መስፈርት በማሟላት ትምህርትና ስልጠና ከመጀመሩ በፊት ከኤጀንሲው ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

2) የተቋሙ አመራርና አደረጃጀት

ሀ) ተቋሙ በዲግሪ ደረጃ ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችለው ግልጽና ለደረጃው የሚመጥን ድርጅታዊ መዋቅር፣

ለ) ለዲግሪ ፕሮግራም ራሱን የቻለ አደረጃጀትና የአስተዳደር ስርዓት፣

ሐ) የተቋሙ በጀት ለሚሰጠው ግልጋሎት በቂና አስተማማኝ የሆነ፣

መ) በሚፈለገው ብዛትና ዓይነት በስልጠናውና በአገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩ በቂ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እና

ሠ) የእያንዳንዱን ክፍልና ሰራተኞች የሥራ ድርሻ በጽሁፍ በተደገፈ ሰነድ የተቀመጠ መሆን ይኖርበታል።

## 3) መምህራንን በተመለከተ

ሀ) በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ለአንድ ክፍል (ከ40-50) ተማሪዎች ለሚሰጡ አብይ (Major Courses) ኮርሶች፣ ለመጀመሪያ፣ ለሁለተኛ፣ ለሶስተኛ፣ ለአራተኛ፣ ለአምስተኛ እና ለስድስተኛ ዓመት እንደቅደምተከተሉ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት እና ሰባት በሁለተኛ ዲግሪና አንድ አንድ በመጀመሪያ ዲግሪ (ረዳት ምሩቅ) ቋሚ መምህራን ሊኖሩ ይገባል።

ለ) የእያንዳንዱ መምህር ሣምንታዊ ጫና በመደበኛው ክፍለ ጊዜ ከ12 ክሬዲት አወር የበለጠ መሆን የለበትም።

ሐ) በተቋሙ የሚያስተምሩ መምህራን በሙሉ የፔዳጎጂ ስልጠና የወሰዱ ሊሆን ይገባል።

መ) አብይና ደጋፊ ኮርሶችን የሚያስተምሩ መምህራን ሁሉም የማስተርስና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፣

ሠ) ተቋሙ ምጣኔው 33 ከመቶ ያልበለጠ ጊዜያዊ መምህራን ሊኖሩት ይችላል።

ረ) የመምህር ተማሪ ጥምርታ እንደ ፕሮግራሙ የሚለያይ ሆኖ በአማካይ 1:25 ሊሆን ይገባል፣

ሰ) ለተግባር ኮርሶች በአንድ (ቤተሙከራ፣ ወርክሾፕ፣ ወዘተ) ከ25 ተማሪዎች መብለጥ የለበትም፣

ሸ) ተቋሙ በቋሚነት ለቀጠራቸው መምህራን አስፈላጊውን መረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፣

ቀ) ከውጭ የተገኘ ዲግሪ ከሆነ የአቻ ግመታ ተሰርቶ መቅረብ አለበት።

በ) የተቋሙ መምህራን ምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጡበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል።

## 4) የስርዓተ ትምህርት ቀረጻ ሂደት እና ተገቢነት

ማንኛውም ተቋም ለሚሰጠው ትምህርትና ስልጠና በአግባቡ የተቀረጸ ስርዓተ ትምህርት ያለው ሆኖ፡-

ሀ) የትምህርት ዓይነቱ ከአገር ፍላጎት ጋር የተገናዘበ፣ አግባብነት ያለው፤ ሰልጣኙን ለስራ የሚያዘጋጅና ችግር ፈቺ ዜጋ የሚያፈራ፤

ለ) የትምህርት ዓይነቱ ዓላማዎችና የምሩቃን ፕሮፋይል በግልጽ የተቀመጠ፤

ሐ) ለእያንዳንዱ ኮርስ የተሟላ ዓላማ፣ መግለጫ (course description)፤ የማስተማሪያና የምዘና ዘዴዎችን፤ የውጤት አሰጣጥ የመማሪያ እና ማጣቀሻ መጽሐፍት ዝርዝር የያዘ፣

መ) እንደትምህርቱ ዓይነት በቂ ቁጥር፤ ዓይነትና አመጣጠን ያላቸው አብይ፤ ደጋፊና መሰረታዊ ኮርሶች፤

ሠ) የስርዓተ ትምህርቱን አፈጻጸም የሚከታተል ተገቢ አደረጃጀት፤

ረ) ትምህርቱና ስልጠናው ሴሚስተርን መሰረት አድርጎ የሚሰጥ መሆኑ፤

ሰ) በየሴሚስተሩ (16 ሳምንት) በመደበኛ መርሃ-ግብር የሚሰጠው የክሬዲት አወር መጠን ከ18 ክሬዲት አወር የማይበልጥ እና አስገዳጅ በሆኑ ሁኔታዎች የክሬዲት አወር መጠኑ በተቋሙ የአካዳሚክ ኮሚሽን ወይም ሴኔት ውሳኔ በቃለ ጉባዔ ተደግፎ እስከ 21 ክሬዲት አወር ከፍ ሊል የሚችል መሆኑን፣

ሸ) ለዲግሪ ፕሮግራሞች መሰጠት ከሚገባው የክሬዲት አወር መጠን አብይ ኮርሶች ከጠቅላላው ክሬዲት አወር በአማካይ ከ76 በመቶ ያላነሰ ድርሻ መኖሩን የሚያሳይ እና

ቀ) አዲስ የትምህርት ዓይነት ለመክፈት የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት፣ በዐውደ ጥናት የተደገፈና የባለድርሻዎችን አስተያየት ያካተተ መረጃ መቅረብ ይኖርበታል።

## 5) ቤተ-መጻሕፍት እና የቤተ መጻሕፍት ግብዓቶች

ሀ) አጠቃላይ የተማሪውን ቁጥር ቢያንስ 25 ከመቶ በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችል እና በተማሪ 1.5 ካ.ሜ የተመጠነ የቦታ ስፋት ያለው፣

ለ) በቂ ብርሃን ያለውና አየር ማስገባት የሚችል፣

ሐ) በኢንሳይክሎፔዲያ፣ በመዝገበ ቃላት፣ በፒሪዮዲካልስ፣ ጋዜጦች ወዘተ. የተሟላ፤

መ) የኢንተርኔት አገልግሎት ያለው፣

ሠ) ቢያንስ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ድረስ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን፤

ረ) በሙያው በቂ የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ያለው የቤተመጻሕፍት ባለሙያና ረዳቶች ያሉት፤

ሰ) ከትምህርቱ ጋር አግባብነት ያላቸው የቅርብ ጊዜ እትም የሆኑ የመማሪያና የማጣቀሻ መጻሕፍትና ሳይንሳዊ ጆርናሎች ያሉት እና

ሸ) ተቋሙ በኢ-ላይብራሪ የተደራጀ ከሆነ የኤሌክትሮኒክ መጽሐፍትና ጆርናሎች፤ እንደታተሙ መጻሕፍትና ጆርናሎች ሊቀጠሩ የሚችሉ ሆነው ተቋሙ ለዚህ አገልግሎት የሚውሉ ኮምፒዩተሮች ያሉት

ሊሆን ይገባል፡፡

## 6) የመማሪያ ክፍሎች

ሀ) በአንድ ተማሪ 1.2 ካሬ ሜትር ምጣኔ በእያንዳንዱ ክፍል ከ40-50 ተማሪዎችን ማስተናገድ የሚችል እና

ለ) በቂ ብርሃንና ቬንትሌሽን ያለው፣ ደረጃቸውን በጠበቁ ቁሳቁሶች የተደራጀ እና ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ የሆነ

ሊሆን ይገባል፡፡

## 7) ቢሮዎችን በተመለከተ

በተገቢው ቁሳቁስ የተደራጁ ለእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል ኃላፊ፣ ለመምህራንና በተቋሙ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት ለሌሎች የሥራ ክፍሎች የሚያገለግሉ ቢሮዎች ሊኖሩ ይገባል።

## 8) የቤተ-ሙከራ፣ የዲሞንስትሬሽን፣ የወርክሾፕ ክፍሎች እና ግብዓቶች፣

ሀ) በተገቢው ግብዓቶች የተደራጁ በተማሪ 3.0 ካሬ ሜትር ቤተሙከራና የዲሞንትሬሽን ክፍል፣ 2.2 ካሬ ሜትር የቋንቋ ቤተሙከራ፣ 5.0 ካሬ ሜትር የድሮዊንግ ክፍል እና 6.0 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ወርክሾፕ፣

ለ) ለቤተሙከራ፣ ወርክሾፕ እና ዲሞንስትሬሽን ክፍሎች ከሥልጠናው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ረዳት ወይም ቴክኒሺያን እና

ሐ) ለሕክምናና የጤና ሣይንስ ፕሮግራሞች ልምምድ ከሚካሄዱባቸው ሆስፒታሎች ወይም ጤና ጣቢያዎች ጋር ሊያሰራ የሚችል መረጃ

ሊኖር ይገባል፡፡

## 9) የኮምፒውተር ማዕከሎች

ሀ) በኮምፒውቲንግ ሳይንስ፣ በማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ተዛማጅ ትምህርቶች ሥልጠና የሚያካሂድ ተቋም ለኔትወርኪንግና እንደየስልጠና መስኩም ለጥገና ጭምር የሚያገለግሉ ወርክሾፖችን፣

ለ) ከሰርቨር ጋር እና እርስ በእርስ የተገናኘ (Server based network) እና የኢንተርኔት አገልግሎት የሚሰጥ የኮምፒውተር ማዕከል እና

ሐ) ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች መሰረታዊ የኮምፒውቲንግ ኮርሶችን ለመስጠት በተመሳሳይ መልኩ የተማሪዎችን ቁጥር ግምት ውስጥ ያስገባ የኮምፒውተር ማዕከላትን

ማደራጀት ይጠበቅበታል።

## 10) ፖሊሲዎች ደንቦችና መመሪያዎች

ማንኛውም የእውቅና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርብ ተቋም በአግባቡ የተዘጋጁና የተሟሉ፣

ሀ) የአካዳሚክ ደንብ የተማሪ ቅበላን፣ ምዝገባን፣ መልሶ መቀበልን፣ የትምህርት ጊዜን ኮርሶችን፣ የሴሚስተር ጫናን፣ ምዘናንና ለምረቃ የሚያበቁ ሁኔታዎችን፣

ለ) የክፍያንና የተመላሽ ገንዘብ አመላለስ፣

ሐ) የመምህራን የቅጥር ሥርዓት፣ መብትና ግዴታ፣

መ) የተማሪዎች መብትና ግዴታ፣

ሠ) የተማሪዎች ጋይዳንስና ካውንስሊንግ እና

ረ) የድጋፍ ሰጪና የአስተዳደር ሠራተኞች የቅጥር፣ ዕድገት፣ ስንብት፣ ወ.ዘ.ተ ደንቦች ማቅረብ አለበት፡፡

11) **የቦታ ስፋት ደረጃዎች**

አንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሕንፃ ሲገነባ ወይም ሲከራይ ለአንድ ተማሪ የሚያስፈልገውን የቦታ መጠን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

## 14. የማታ ትምህርትን በተመለከተ

1) ማንኛውም በማታ መርሃ-ግብር ለማሰልጠን የእውቅና ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርብ ተቋም ለመደበኛው የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ተማሪዎችን ተቀብሎ ማሰልጠን ይችላል፡፡
2) በማታ መርሃ-ግብር በአንድ ሴሚስተር ከ12 ክሬዲት አወር የበለጠ መሰጠት አይችልም፡፡
3) በማታው መርሃ-ግብር የሚሰጥ ትምህርት የሚወስደው የስልጠና ጊዜ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተቀመጠውን መሰረት ባደረገ መልኩ ይሆናል።

## 15. የዕውቅና ፈቃድ ስለመስጠት

1) ኤጀንሲው በአንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1-11 የተቀመጡ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ገምግሞ በማረጋገጥ የዕውቅና ፈቃድ ይሰጣል።

2) ተቋሙ የዕውቅና ፈቃዱን በወሰደበት ሴሚስተር ተማሪዎችን መመዝገብ ካልቻለ ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት ለኤጀንሲው ማሳወቅ ይኖርበታል።

# ክፍል አራት
# የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት አሰጣጥ
# መገምገሚያ መስፈርቶች

## 16. የዕውቅና ፈቃድ እድሳት አገልግሎት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

ትምህርትና ስልጠና ሲሰጥ የቆየ ተቋም ትምህርትና ስልጠናውን ለመቀጠል አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የያዘ የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ማመልከቻ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡ ማመልከቻው በክፍል ሶስት አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ1፣ 2 እና 3 የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1) የትምህርት ግብዓቶችና መገልገያዎች አሁን ያሉበትን ደረጃ የሚገልጽ ሪፖርት፣
2) የተቋሙ የአካዳሚክ፣ የቴክኒክና የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ዝርዝር፣
3) በየዓመቱ ተቋሙ በሚሰጠው በእያንዳንዱ የትምህርት መስክ የተመዘገቡ ተማሪዎች ዝርዝር፣
4) በኦዲተር የተመረመሩ የመጨረሻዎቹን ሁለት ዓመታት የሂሳብ ሪፖርቶች፣
5) የየስድስት ወር የአፈጻጸም ሪፖርት፣
6) የጥራት ማጎልበት ዩኒት ዓመታዊ ሪፖርት፣
7) የምርምርና ስርፀት የስራ ክንውን ሪፖርት እና
8) ተቋሙ ካለው የፕሮግራሞች ዓይነት አኳያ ለትምህርት ጥራት መሻሻል በያዘው የአምስት ዓመት እቅድ መሰረት መዋዕለንዋይ እያፈሰሰ መሆኑን የሚያሳይ ሪፖርት መቅረብ አለበት።

## 17. የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1) የተቋሙ አደረጃጀትን በተመለከተ

በአንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ በአደረጃጀቱ ላይ ያደረጋቸው ለውጦችን/መሻሻሎችን የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

**2) የመምህራን ብዛትና ስብጥር**

በአንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 3 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

ሀ) ተቋሙ ለመጀመሪያ ጊዜ የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ሲያቀርብ በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ለሚሠጡ ኮርሶች ከ40-50 ተማሪዎችን ለሚይዝ ክፍል በሙያው ቢያንስ ለሶስት፣ ለአራት፣ ለአምስት እና ለስድስት ዓመት የቆይታ ጊዜ ላላቸው የትምህርት ዓይነቶች እንደየቅደም ተከተላቸው አራት፣ አምስት፣ ስድስት እና ሰባት የሁለተኛ እና አንድ አንድ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ያስፈልጋሉ።

ለ) የተቋሙ መምህራን ምርምር የሚሰሩበትና የሕብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጡበት ስርዓት ተጠናክሮ ሊተገበር ይገባል።

ሐ) ተቋሙ ለሁለተኛ ጊዜ የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ሲጠይቅ የስልጠናና የምርምር ተግባራትን በተፈለገው የጥራት ደረጃ ማካሄድ እንዲቻል በየስልጠና መስኩ 25 ከመቶ የሦስተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን እንዲኖሩት ይጠበቃል። በዚህ መሰረት በሙያው ለሶስት፣ ለአራት፣ ለአምስት እና ለስድስት ዓመት የቆይታ ጊዜ ላላቸው የትምህርት ዓይነቶች እንደየቅደም ተከተላቸው ሶስት፣ አራት፣ አምስት እና ስድስት የሁለተኛ እና አንድ አንድ የሦስተኛና የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ያስፈልጋሉ።

**3) ስርዓተ ትምህርትን የማሻሻል ሂደት**

በአንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 4 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ በሥርዓተ ትምህርት ላይ ያደረጋቸውን ለውጦች የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

**4) ቤተ-መጻሕፍትና የቤተ መጻሕፍት ግብዓቶች**

በአንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 5 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ በቤተ መጻሕፍት አደረጃጀትና የመጻሕፍት ክምችት ላይ ያደረጋቸውን ለውጦች የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

### 5) ፊዚካል ግብዓቶች

በአንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 6፣ 7፣ 8 እና 9 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ በፊዚካል ግብዓቶች ላይ ያደረጋቸውን ለውጦች የያዘ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

### 6) ደንቦችና መመሪያዎች

በአንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 10 የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተቋሙ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ ስለመሆናቸው የሚገልፅ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

### 7) ግለ-ግምገማ

ኤጀንሲው ባዘጋጀው የትኩረት ነጥቦች መሰረት ግምገማ በማድረግ የግለ ግምገማ ሰነዱን በማዘጋጀት የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ ከማቅረቡ ከአንድ ዓመት በፊት ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል።

## 18. የሂደት ግምገማ

በተቋሙ የሚካሄዱት የመማር ማስተማር፣ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት እንቅስቃሴዎች በተጨባጭ ይገመገማሉ፣

1) የመማር ማስተማር ሂደት

- ሀ) የተለያዩ አሳታፊና ተማሪ ተኮር የመማርያ ዘዴዎችን መጠቀሙ፣
- ለ) በተግባር የተደገፈ ትምህርት መሰጠቱ፣
- ሐ) የታቀደ አካዳሚክ የማማከር ስራ መሰራቱ፣
- መ) የመምህራን ግምገማ ስርዓትና አፈጻጸም እና የተወሰዱ የእርምት እርምጃዎች በመረጃ የተደገፉ መሆኑን፣
- ሠ) የኮርስ ሽፋንና ስርዓተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ እና
- ረ) የተቋሙ መምህራን ሙያዊ ስነምግባር መከታተያ ስርዓት የሚታዩ ይሆናል።

2) ምዘናና የምዘና ስርዓት

ሀ) ፈተናዎች የሚወጡበት፣ የሚጸድቁበት እና የአስተዳደር ስርዓት፣

ለ) ተከታታይ የምዘና ስርዓት፣

ሐ) ቋሚ የውጤት አሰጣጥ ስርዓት እና

መ) ምዘናው በስርዓተ ትምህርቱ ከተቀመጡት ዝርዝር ዓላማዎች ጋር አብሮ የሚሄድ መሆኑ ይታያል።

3) ለስርዓተ ትምህርቱ ወቅታዊ የሆነ የማሻሻል ስርዓት ስለመኖሩ፣

4) ለተማሪዎች የድጋፍ አገልግሎት፣

5) የጥናትና ምርምር እና የፕሮጀክት ስራዎች

ሀ) የመመረቂያ ጽሁፍ ወይም የፕሮጀክት ስራ የማማከር ሂደት፣

ለ) የጥናትና ምርምር ፕሮፖዛል አዘገጃጀት፣ ግምገማና አጸዳደቅ ስርዓትና የበጀት አጠቃቀም ስርዓት እና

ሐ) የምርምርና ስርፀት እና የገበያ ትስስር ስርዓት ስለመኖሩና መተግበሩ ይታያል።

6) የመምህራን ልማት

ሀ) የመምህራን ልማት እቅድና አፈጻጸም እና

ለ) መምህራንን ከአዳዲስ ቴክኖሎጂ እና እውቀቶች ጋር የማስተዋወቅና የማብቃት ስራ ስለመተግበሩ ይታያል።

7) ቅጥርና እድገት

የመምህራንና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የቅጥርና እድገት መመዘኛዎች እና አተገባበራቸው የሚታዩ ይሆናል።

## 19. የውጤት ግምገማ

ተቋሙ በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎቶች ያስገኛቸው ውጤቶች ይገመገማሉ። በዚህ መሰረት ተቋሙ፡-

1) ገበያው የሚፈልገውን ምሩቅ ማፍራቱን፣

2) ያከናወናቸው ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎች፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራና ሽግግሮች እና የታተሙ ጽሁፎችን፣
3) ለማህበረሰቡ ያበረከተው አገልግሎቶችን፣
4) ስራ የመፍጠር ብቃትና በኢንዱስትሪው ተቀጣሪ የሆኑ ምሩቃንን ማፍራቱ እና
5) ያካሄደው የቀጣሪዎች የእርካታ ዳሰሳ ውጤት የሚታዩ ይሆናል።

## 20. የእውቅና እድሳት ፈቃድ ስለመስጠት

በአንቀጽ 13፣ 17፣ 18 እና 19 የተዘረዘሩት መሟላታቸውን በማረጋገጥ ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ እድሳት ይሰጣል።

## 21. ሌሎች የአዋጁን ድንጋጌዎች በተመለከተ

የእውቅና ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣ የዕውቅና ፈቃድ ስለመከልከል፣ የእውቅና ፈቃድ እና የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ያገኙ ተቋማትን ስለማሳወቅ እና አቤቱታ ማቅረብን በተመለከተ በአዋጁ አግባብነት ባላቸው አንቀጾች በተደነገገው መሰረት ይሆናል።

## እዝል ሀ

## የትምህርት ጥራትና አግባብነትን ለማሻሻል በተቀመጠው አቅጣጫና የአፈፃፀም መመሪያ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ

### አጠቃላይ አቅጣጫ

መንግስት በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ አቅጣጫ ሲያስቀምጥ የዘርፉ ዋነኛ ትኩረት ኢኮኖሚው የሚፈልገውንና በገበያው ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ሀይል ማፍራት ሊሆን እንደሚገባ መወሰኑ ይታወሳል። በዚህ መሰረት ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጡት ትምህርትና ስልጠና በሳይንስና ቴክኖሎጂ (70%) እና በሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ (30%) ምጣኔ የተከተለ ሊሆን ይገባል። በአሁኑ ሰዓት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሞላ ጎደል ምጣኔውን ጠብቀው የሚሠጡበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ይሁን እንጂ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እዚህ ደረጃ ላይ አልደረሱም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በተለያዩ ጊዜያት ከተወሰዱ የግምገማ ውጤቶችና ከተገኙ መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው ተቋማት እየሰጡት ያለው ትምህርት በተለያየ የጥራት ደረጃ ላይ ይገኛሉ። ስለሆነም የትምህርት ተቋማቱ በተሰማሩበት መስክ ትምህርቱን በጥራት እየሰጡ መሆናቸውንና በተሰጠው የሰው ሃይል ልማት አቅጣጫ እየገቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል። በዚህም መሠረት የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እስካሁን ባላቸው የትምህርት አግባብነትንነና የጥራት ደረጃን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች በተቀመጡት ሶስት ደረጃዎች ተቋማቱን መክፈል አስፈልጓል፡፡

ደረጃ 1፡ ጥራት ያለው ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል፣ ብቃትና ዝግጁነት ያላቸውና መንግስት የበለጠ የሚያበረታታቸው ተቋማት፣

ደረጃ 2፡ በተወሰነ እገዛና ክትትል እየተሰጣቸው ብቃታቸው ወደሚፈለገው ደረጃ ሊመጡ እንደሚችሉ የሚታመንባቸውና ደረጃ በደረጃ እየተጠናከሩ የሚሄዱ ተቋማት፣

ደረጃ 3፡ የትምህርት ጥራትና አግባብነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ዝግጁነቱና ብቃቱ የሌላቸውና በዚህ ሥርዓት ለመቀጠል የማይችሉትን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ናቸው።

እነዚህን ደረጃዎች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል።

ለዚህም የመጀመሪያ የማስተካከያ እርምጃ ባሉ የግምገማ ውጤቶችና ከተገኙ መረጃዎች በመመስረት የከፋ የጥራት ችግር የሚታይበትን የርቀት ትምህርት እና ከሞላ ጎደል ችግሩ ሰፍቶ የሚታይባቸውን የሕግና የመምህራን ትምህርት ላይ ማስተካከያ መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም፣

1. ሁሉም የመንግስትና የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በ70፡30 የፕሮግራም ምጣኔ መሠረት ገበያው የሚፈልገውን የአገራችንን የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲያፈሩ ይደረጋል፣
2. የመምህራንና የሕግ ባለሙያዎች ስልጠና በመንግስት ተቋማት ብቻ ይከናወናል፡፡
3. የርቀት ትምህርትን በተመለከተ

3.1 በርቀት ትምህርት የተሰማሩ ሁሉም ተቋማት በቅድመ ምረቃና በድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች  በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎችን ብቻ በብቃት ያስጨርሳሉ።

3.2 በርቀት ትምህርት በማስተማር ላይ ያሉ ተቋማት አዲስ ፕሮግራምና ቅበላ ማካሄድ የሚችሉት አሁን በሚሰጡት መርሃ-ግብሮች ላይ በብቃት ለማሰልጠን የሚያስችላቸውን መሠረታዊ ማሻሻያ ሙሉ በሙሉ ማድረጋቸው በተግባር ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ለዚህም አግባብ ባላቸው አካላት አፈፃፀማቸው በዝርዝር እየተገመገመ በሚደረስበት ውሳኔ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

3.3 በቅድመ ምረቃ በርቀት ትምህርት ሲያሰለጥኑ የቆዩ ተቋማት በመደበኛ ፕሮግራም ማሰልጠን ከፈለጉ በዚህ መስክ መስፈርቱን ሲያሟሉ እውቅና ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ሆኖም በሁለት ዓመት ውስጥ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገው ወደተቀመጠው የምጣኔ ሥርዓት መግባት ይጠበቅባቸዋል። ለዚህም በስድስት ወራት ውስጥ ዝርዝር የሥራ እቅድ (Business plan) እንዲያቀርቡ ይጠበቃል።

3.4 የሁለተኛ ዲግሪ ፕሮግራም ለመስጠት በቅድሚያ የመጀመሪያ ዲግሪ በተመሳሳይ የስልጠና መስክ ሁለት ጊዜ አስተምሮ ማስመረቅ የሚጠይቅ ቢሆንም በርቀት ትምህርት የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ሲሰጡ የቆዩ ተቋማት ብቃታቸው እየተረጋገጠ በመደበኛ ፕሮግራም መስጠት ይችላሉ።

3.5 በድህረ ምረቃ የርቀት ትምህርት ከመንግስት ጋር ውል ገብተው በመስጠት ላይ ያሉ ተቋማት በውሉ መሠረት መተግበራቸው እየተገመገመ ሥልጠናውን ያካሂዳሉ። ይህን በተመለከተ ራሱን የቻለ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ይወጣለታል፡፡

4. አዲስ የእውቅና ጥያቄዎችን በተመለከተ

4.1 ተቋማት የአገሪቱን የሰው ኃይል ፍላጎት ባማከለ መልኩ ገበያው የሚፈልገውን የሰው ኃይል በሳይንስና ቴክኖሎጂ (70%) በሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ (30%) የፕሮግራም ምጣኔ መሠረት የእውቅና ጥያቄ ሲያቀርቡ ተገምግመው እውቅና የሚሰጣቸው ይሆናል።

4.2 አንድ ተቋም የሚሰጣቸውን ስልጠናዎች ሙሉ በሙሉ በቴክኖሎጂ ወይም በተፈጥሮ ሳይንስ መስክ ማድረግ ከፈለገ የተቀመጠውን የእውቅና መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚሰጡት ስልጠናዎች በጤናና በግብርና የሙያ መስኮች ከሆኑ የሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ለኤጀንሲው በሚያሳውቁት የአጭርና የረጅም ጊዜ የሰው ኃይል ፍላጎትና የስልጠና መስኮች ትኩረት መሠረት በማድረግ የእውቅና ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

5. እውቅናና እውቅና እድሳትን በተመለከተ

5.1. በ2002 ዓ.ም. እውቅና አግኝተው ነገር ግን ሥልጠና ያልጀመሩ ተቋማት እውቅናቸው ይከበራል፤ ይሁንና ወደ ሥራ ሲገቡ በሁለት ዓመት ውስጥ በተራ ቁጥር 4 የተቀመጠውን አቅጣጫ ለማሟላት የሚያስችላቸውን እቅድ በስድስት ወራት ውስጥ እንዲያቀርቡ ይጠበቃል፡፡

5.2. የእውቅና ጥያቄ አቅርበው ነገር ግን እውቅናቸው ያልታየላቸው ተቋማት እውቅናቸው በተሻሻለው የእውቅና መመሪያ መሠረት የሚታይላቸው ይሆናል።

5.3. አንድ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ኤጀንሲው ያወጣቸውን የጥራት ደረጃዎች ጠብቆ መሥራቱ ሲረጋገጥ እውቅና ባገኘባቸው የሥልጠና መስኮች የተማሪዎችን ቁጥር መጨመር ይችላል።

5.4. የእውቅና እድሳት ፈቃድ ጠይቀው እውቅናቸው ያልታደሰላቸው ተቋማት ብቃታቸው ተገምግሞ የእውቅና ፈቃዳቸው ሊታደስላቸው ይችላል። ይሁን እንጂ በ6 ወራት ውስጥ ዝርዝር የስራ እቅድ እንዲያቀርቡ ይደረጋል። በሁለት ዓመት (2003-2004 ዓ.ም) ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ዝግጅት በማካሄድ በሶስተኛው ዓመት (2005 ዓ.ም) ሙሉ በሙሉ በመንግስት የትኩረት አቅጣጫ የሥልጠና መስኮች ሥልጠና መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ከቅድመ እውቅና የእውቅና ፈቃድ ጥያቄ አቅርበው ያልታየላቸው ተቋማትም በተመሳሳይ መልኩ ይስተናገዳሉ።

6. አዲስ ቅርንጫፍ መክፈትን በተመለከተ

አዲስ ተቋም ማቋቋምና አዲስ ቅርንጫፍ ወይም አዲስ ፕሮግራም መክፈት በተጨባጭ አንድ ናቸው። በመሆኑም የሚከፈቱ የሥልጠና መስኮች በሳይንስና ቴክኖሎጂና በሶሻል ሳይንስ ሂውማኒቲ የፕሮግራሞች ምጣኔ ይሆናል።